**<u>ከአውስትራሊያ ፐርዝ የአማራ ሴቶችና የአማራ ዎጣቶች ማህበር የተሰጠ መግለጫ</u>**

ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ/ም በአማራ ክልል ከፍተኛ አመራሮች ላይ ግድያና እስራት ተፈፅሟል። በሰፊው የአማራ ሕዝብ ላይም እስካሁኑ ሰዓት ድረስ ወረራ፣ ግድያ፣ ማፈናቀል፣ አፈናና ማስፈራራት እየተፈጸመበት ነው። ስለዚህ እኛ በአውስትራሊያ ፐርዝ የአማራ ሴቶችና የአማራ ወጣቶች ማህበራት በአማራው ወቅታዊይ ሁኔታ ላይ በሰፊው ተወያይተን የሚከተለውን መግለጫ አውጥተናል።

1. ከአዲስ አበባ እና ከኦሮሚያ የሚታፈኑ አማራዎች በማንነታቸውና በአማራ መሪነታቸው ብቻ ስለሆነ ይህ የግፍ እርምጃ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲቆም ለክቡር ጠ/ም ዶ/ር አቢይ መንግስት ጥሪያችን እናቀርባለን
2. በፌደራል ትዛዝ በልዩ ልዩ የሀገሪቱ ክልሎች ታፍነው የተያዙ አማራዎች በአስቸኳይ እንዲፈቱ እንጠይቃለ
3. በአማራ ክልል የተሰማራው መከላከያ ክልሉን ባስቸኳይ ለቆ እንዲወጣ እየጠየቅን በአንፃሩ ደግሞ የአማራ ክልል መስተዳድር የህዝባችን ሉዓላዊነት እንዲያስከብር አጥብቀን እንመክራለን
4. ሰኔ 15 ቀን 2011 በግፍ የተገደሉት የአማራ መሪወች ግድያ በነፃና ገለልተኛ አካል በአሰቸኳይ ተጣርቶ ለመላው ሕዝባችን እንዲገለፅ እንጠይቃለን
5. ሰኔ 15 ቀን 2011 በአማራው ላይ የተቃጣው ወረራና ህለውናውን ጨርሶ የማጥፋት ዘመቻ ስለሆነ አዴፓ/ብአዴን ጉዳዩን በሚገባ ተመልክቶ ህዝቡንና ልዩ ልዩ የአማራ ድርጅቶችን በማስተባበር ከአማራ ጠል ቡድኖችና ግለሰቦች የጥፋት ዘመቻ አማራውን እንዲከላከል በአክብሮት እናሳስባለን
6. በአማራው ሕዝብ ላይ ከረጅም አመታት ጀምሮ እስካሁን ድረስ በአማራ-ጠል ሐይሎችና ተባባሪዎቻቸው ግድያ፣ ዘረፋ፣ ማፈናቀል...ወዘተ ግፍ ተፈፅሞበታለ። ይህ ማብቂያ ያለተገኘለት አማራውን የማጥፋት ዘመቻ አሁንም በኢህአዴግ የሚመራው የጠ/ም ዶ/ር አቢይ መንግስት በተረኝነት ሺፋን እያራመደው ነው። ስለሁነም በአማራው ላይ የሚፈፅመውን ኢ-ሰባዊ ድርጊት ለሰው ልጅ ደሕንነት የቆሙ ዓለም አቀፍ የሰባዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችና መንግስታት በፅኑ እንዲያወግዙት ጥሪያችን እናቀርባለን

በመጨረሻም ለተጎዱት ሟቾችና ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ለመላው የአማራ ሕዝብ መፅናናቱን እንዲሰጥልን እየተመኘን በውስጥም ሆነ በውጭ የምንገኝ የአማራ ተወላጆች ከመቸውም በበለጠ ሁኔታ ሕዝባችን ከሚደርስበት ጠቅላላ ጥፋትና ወረራ ለመከላከል የበኩላችን አስተዋፅኦ ለማድረግ ጠንካራ አደረጃጀትና የመረጃ ልውውጥ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። የጉዳዩን አሳሳቢነት በአስቸኳይ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መንቀሳቀስና በጋራ ተግባራዊ ማድረግ ስላለብን ለሁሉም አማራ የትግል ትብብር ጥሪያችን በዚሁ አጋጣሚ እናቀርባለን

አንድ አማራ ለሁሉም አማራ
ሁሉም አማራ ለአንድ አማራ

በፐርዝ አውስትራሊያ የአማራ ሴቶችና የአማራ ወጣቶች ማህበር